MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት
8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
Tel: (202) 230 - 9423 ▪ Fax:

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት    እሑድ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፪ሺህ፮ ዓ.ም.    ቅፅ ፪ ፣ ቁጥር ፳፯

# ፕሮፌሠር መሥፍን ወልደማርያም በዐማራው ቁስል ላይ ጨው ነሰነሱ! የ«ዐማራ የለም» አቋም የክህደት ወይስ የመሣት?

ሰሞኑን ፕሮፌሠር መሥፍን ወልደማርያም «ሸገር» ከተሰኘ በኤፍ.ኤም. 102.1 (FM 102.1) ከአዲስ አበባ መርኃግብሩን ከሚያሠራጭ የሬድዮ ጣቢያ ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ «ዐማራ» የሚባል ነገድ በኢትዮጵያ አለመኖሩን ልባቸውን ነፍተው ሲናገሩ ተደምጠዋል። ፕሮፌሠር መሥፍን በዚህ ቃላቸው፣ በ፲፱፻፹፫(1983)ዓ.ም. ከሟቹ የትግሬ-ወያኔዎች መሪ መለስ ዜናዊ ጋር በቴሌቪዥን ቀርበው ስለ ዐማራው ነገድ ያለመኖር ያንጸባrmቁትን አቋም አፅንዖት በመስጠት በድጋሚ አረጋግጠዋል።

ዐማራ የሚባል ነገድ በኢትዮጵያ ውስጥ «አለ» ወይስ «የለም» ብሎ፣ በላ! ልበልሃ! ወደሚል እጅግ የወረደ ክርክር የሚገባ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው የለም። እንዲህ ዓይነት ክርክር ውስጥ የሚገባ ሰው፣ ኃሣቡ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ የማይችል የፕሮፌሠር መሥፍን ዓይነቱ ሰው ብቻ ነው። ለነገሩ በዚህ የቀን ቅዠት አቋም የሚፀና ካለ ከፕሮፌሠር መሥፍን ሌላ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው ይገኛል ተብሎ አይታሰብም። የፕሮፌሠር መሥፍንም ክርክር ጭፍን ክህደት ወይም መሣት (መጃጀት) አልያም ቀቢፀ-ተስፋ የተሞላው ቁጭት ከመሆን አያልፍም። የፕሮፌሠር መሥፍን አቋም የክህደት ከሆነ፣ ወላጅ አባታቸውን ዕውቁን ሊቅ አለቃ አስረስ የኔሰውን ከደዋልና የዐማራ ነገድን ኅልውና ከመካድ የሚያግዳቸው የኅሊና ልጓም ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። ከመሣት(መጃጀት) የመነጨ ከሆነ ግን አያድርስ! እንዲህ እስኪሆንስ ፈጣሪን «አታቆዬን» ከማለት ሌላ ምን ይባላል። ከቁጭት ከሆነ ነገሩ ሌላ ነው። በቁጭት የአንድን ታላቅ ሕዝብ መኖር ኅልውና ክዶ ስለዚያ ሕዝብ መከራከር እና መጮህ አይቻልም። የቁጭት ተገቢ መገለጫው «አሻፈረኝ! በቃኝ! ተነስ! ዱሩ ቤቴ በል!» በማለት እንጂ «የለህም! የሚያጠፉህ ሳትኖር ነው!» በማለት አይደለም። የሌለ፣ ኅልው ያልሆነ፣ ሊያደርገው የሚችለው ምንም ነገር የለምና!

ፕሮፌሰር መሥፍን «ዐማራ የሚባል ነገድ የለም» ከሚል መደምደሚያ የደረሱት፣ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ከሦሥቱ በአንዱ ወይም በሁሉም ተያያዥነት እንደሆነ ቀደም ካሉት ድርጊቶቻቸው መገንዘብ ይቻላል። የመጀመሪያው በ፲፱፻፹፫(1983) ዓ.ም. ከሟቹ መለስ ዜናዊ ጋር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ባደረጉት ውይይት ዐማራን እና ክርስቲያንን የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን በመዘንጋት፣ ወይም ሆን ብለው «ክርስቲያን እንጂ፣ ዐማራ የሚባል የለም» ብለው ተከራክረው ስለነበር ያ አቋማቸው ያልተለወጠ መሆኑን እና ዛሬም «በዚያው አቋማቸው የጸኑ ናቸው» ለመባል ከማሰብ የመነጨ፣ ከስህተት ወደ ስህተት የመጓዝ አስተሳሰብ ነው። ሁለተኛው ፕሮፌሠር መሥፍን ክህደት የመታወቂያ ባሕሪያቸው ስለሆነ ትናንት የካዱትን ከ፳፫(ሃያ ሦሥት) ዓመታት በኋላም በክህደቱ የቀጠሉ መሆኑ የሚያመለክት ነው። ይህም ሌላው ግትርና «ያለ እኔ ዐዋቂ የለም» የሚለው የገነገነ አስተሳሰባቸው መገለጫ ነው። ሦስተኛው ከክህደት ባሕሪይ በተጨማሪ በዕድሜ መግፋት ምክንያት የመጣ፣ የኋላን ያለማዬት እና የመሣት አባዜ የገጠማቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። አራተኛው በዘመነ የትግሬ-ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በዐማራው ላይ በተከታታይ እየተፈጸመበት ያለው መገደል፣ መታሠር፣ ከሥራ መፈናቀል፣ ከአገር መባረር፣ መዋረድ እና መንሳቀል እጅግ በዝቶ የግፉ ጽዋ ሞልቶ የሚፈስበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ሆኖም ዐማራው «አሻፈረኝ» ብሎ ወያኔን ግብግብ ከመግጠም ይልቅ የሚሣየውን ሆደ ሠፊነት ከኢዮብ ትዕግሥት በላይ ሆኖ ስላገኙት፥ «ዐማራ የሚባል ነገድ ቢኖር ኖሮ ይህ ሁሉ ጥቃት እና ውርደት ሲፈጸምበት ዝም ብሎ አይመለከትም ነበር! ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ኃይሉን አስተባብሮ ጥቃቱን ይቋቋም ነበር! ባለመኖሩ ነው ይኸ ሁሉ ጥፋት የሚፈጸምበት» ከሚል ቁጭት የደረሱበት ድምዳሜ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ይህ ግን ከዐማራው ባህል፣ ዕምነት፣ አኗኗር፤ ማኅበራዊ ግንኙነት እና የኢትዮጵያዊነት ስሜት ጋር አጣምሮ ለሚያይ ሰው፣ ዐማራው በወያኔ የደረሰበትን ሁለንተናዊ ግፍ እና በደል በአርምሞ በመመልከት ላይ ያለው፣ በደሉ ሳይሰማው ቀርቶ አይደለም። እንዲያውም «የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች» እንዳይሆንበት የትግሬ-ወያኔዎችን ግፍ ለመበቀል ሲል በደልን በበደል መመለስ፣ የትልቂቱን አገሩን የኢትዮጵያን ኅልውና እንዳያፈርስ ኅሊናውን ገዝቶት፣ በሆደ ሠፊነት እና በትዕግሥት ማየቱ፥ ብልኅነቱን፣ አስተዋይነቱን፣ «አድሮ እንየው» ማለቱን፣ ውሸንፍርን እና ጥምዝምዝን አጎንብሶ ማሳለፍ ባህሉ መሆኑን፣ እንጂ፤ ጥቃትን እስከ ዝንተ ዓለሙ የሚቀበል አለመሆኑ ታሪኩ ያስረዳል። «ዐማራ ሰንበሌጥ ነው፤» የሚባለውም እኮ ለዚህ ነው። ማንም እንደሚያውቀው ሰንበሌጥ ኃይለኛ ወዠብ (ነፋስ) ሲመጣበት ለጥ ብሎ ያሳልፋል፣ ወዠቡ ሲያልፍ ይነሣል። ዐማራውም በተደጋጋሚ እና በተከታታይ ሊያጠፉት የተሰለፉትን ኃይሎች ሁሉ ተቋቁሞ እስካሁን የዘለቀው በዚህ መንገድ ነው። ጠላቶቹን የሚያሸንፋቸው በመበቀል ሣይሆን በይቅርታ እና በፍቅር መሆኑን ለአፍታም መዘንጋት አያስፈልግም። የኢትዮጵያዊነት ማገር፣ ዋልታ እና ጭምጭም ሆኖ ለዘመናት የዘለቀውም የፍቅር፣ የአንድነት እና የአብሮነት ስሜቱ የዳበረ በመሆኑ ነው። ይህም በመሆኑ ነው የዐማራው ሥነልቦና በድል ጊዜም ሆነ በጥቃት ላይ እያለ የበላይነቱን እንደጠበቀ እንዲዘልቅ ያደረገው።

ዛሬ ወያኔን እና መሠል ቡድኖችን ያስጨነቃቸው ይኸው የዐማራው የኢትዮጵያዊነት ሥነልቦና የበላይነት አልሰበር በማለቱ ነው። እኒህን ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ሌት ተቀን የሚያባንናቸው ዐማራው ኢትዮጵያዊነትን ማተቡ፣ ዕምነቱ እና የእሱነቱ መገለጫ፤ ሠንደቅ ዓላማውንም ልብሱ፣ ትራሱ እና መጌጫው አድርጎ በዓለም አደባባይ ስለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት የሚያሰማው ድምፅ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያስገመገመ በመጓዙ ነው።

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ይህን መግለጫ ለማውጣት የወሰነው በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነው። አንደኛው ምክንያት ዛሬ በምንኖርበት የቴክኖሎጂ ዘመን አብዛኛው ሰው የሚያምነው የሚያየውን ብቻ ሣይሆን የሚሰማውንም ጭምር በመሆኑ ነው። እንዲያውም ሰው ከሚያየው ይልቅ የሚሰማውን ይበልጥ አምኖ ይቀበላል። ስለሆነም «ፕሮፌሠር መሥፍን እኮ ዐማራ የሚባል ነገድ የለም ብለዋል» ብሎ የሚቀበለው እና የሚያምነው ሰው ቁጥር ቀላል ስለማይሆን፣ ለዚህ ዓይነቱ አድማጭ ዕውነታውን ማሣወቅ አስፈላጊ ይሆናል። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ፥ ምንም እንኳን ጊዜ እየከዳቸው ያሉ ቢሆንም፣ እስትንፋሳቸው እስካለ ድረስ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሌሎች የክህደት ንግግሮችን ከመናገር ስለማይቆጠቡ፣ ፕሮፌሠር መሥፍን «ዐማራ የለም» ሲሉ የካዱትን ክህደት በተጨባጭ መረጃዎች በማሣዬት ለወደፊት

አድማጫቸው እና አንባቢያቸው ከሃዲነታቸውን ከወዲሁ እንዲገነዘብ ለማድረግ ነው። ከዚህ አንፃር የዐማራን ነገድ ከኢትዮጵያ ምድር አልፎ በዓለም ዙሪያ ተሠራጭቶ የሚኖር መሆኑን የሚከተሉት መረጃዎች ያረጋግጣሉ። እነርሱም፡-

- ፩ኛ አካላዊ (ነባራዊነት)፣
- ፪ኛ አማርኛ የተሰኘ ቋንቋ በኢትዮጵያ መኖር እና በስፋት መነገር፣ እንዲሁም
- ፫ኛ የጽሑፍ፣ የቃል (ድምፅ) እና የምሥል ማስረጃዎች ናቸው።

## ፩ኛ. <u>አካላዊ (ነባራዊነት)</u>

አካላዊ ወይም ነባራዊነት ስንል፥ በእጅ የሚዳሰስ፣ በዐይን የሚታይ፣ ግዙፍ፣ ራሱን «ዐማራ ነኝ» ብሎ የሚገልጽ ሰው የተሰኘ ፍጡር በኢትዮጵያ ምድር በስፋት ተሰራጭቶ የሚኖር ሕዝብ ማለታችን ነው። ይህ ሕዝብ ቀደም ሲል ክርስትና ወደ አገራችን ሲገባ ቀድሞ የተቀበለ በመሆኑ ከክርስትና ኃይማኖት ጋር አያይዞ የራሱን ማንነት የሚጠራ፤ ሌሎችም «ዐማራ» ሲሉ «ክርስቲያን የሆነ» ማለታቸው እንደሆነ አድርገው የሚገልጹት፣ በኋላም በጊዜ ሂደት ወደ አገራችን የገቡ ዕምነቶችን ሳይቃወም፣ መቻቻልን መርሑ አድርጎ የተቀበለ እና ከእርሱም ውስጥ የተወሰነው ክፍል የክርስትና ኃይማኖቱን በመተው ሌሎች ዕምነቶችን በመከተል የኖረ፣ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ነገዶች በቁጥር ከፍተኛውን መጠን የያዘ ማለታችን ነው።

ማንም በግልጽ ሊገነዘበው እንደሚችለው፣ ቋንቋ ከሰው በፊት አልተፈጠረም። ቋንቋ ከሰው ልጅ ኅልውና በኋላ የተከተለ የሰዎች የጋራ የመግባቢያ መሣሪያ ነው። ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይዳብራል፣ ይሞታል የሚባለውም ከሰዎች መኖር ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ ነው። በሌላም በኩል ቋንቋ ባህልም ነው። ከጥንት ጀምሮ የቁጥር መጠኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የሄደ እና ራሣቸውን «ዐማራ ነኝ» በሚሉ ተወላጆች የጋራ ማንነት የተገነባ ነገድ አለ። እነህ ሰዎች አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ፣ ካለ አማርኛ ቋንቋ ሌላ ቋንቋ መናገር የማይችሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው። በመሠረቱም የአማርኛ ቋንቋን መግባቢያ እና መገልገያ ያደረገ ሕዝብ ሣይኖር የአማርኛ ቋንቋ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ወይም ነገዶች እና ጎሣዎች አንድ ተብለው መቆጠር ሲጀምሩ በቅድሚያ በማንም ሰው አዕምሮ ውስጥ ድቅን የሚለው ዐማራ ነው። ስለዚህ በማንነቱ ከኢትዮጵያ ኅልውና ጋር በጥብቅ የተሣሰረ «ዐማራ» የሚባለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አካል ኅልውና መካድ ኢትዮጵያን ከመካድ ተለይቶ አይታይም።

ሌላው አካላዊ ማስረጃ «ዐማራ ሳይንት» የተባለው እና በላኮመልዛ(ወሎ) ክፍለሃገር የሚገኘው የአውራጃ ስም ነው። «ዐማራ» የሚባል ነገድ ሳይኖር፣ በዐማራ ስም የሚጠራ የቦታ ስም ሊኖር አይችልም። በሌላም በኩል ከጥንት ጀምሮ በጌምድርና ስሜን(ጎንደር)፣ ጎጃም፣ ሸዋ እና ላኮመልዛ(ወሎ) የተሰኙ የኢትዮጵያ መልከዐ-ምድር አካል የሆኑ ክፍለ-ሀገሮች አሉ። የነዚህ ክፍለ-ግዛቶች አብዛኛው ነዋሪ ሕዝብ ዐማራ በመሆኑ «ዐማራ የሚኖርባቸው» ተብለው የሚታወቁ ናቸው። ከዚህም አልፎ በዘመነ ትግሬ-ወያኔ «የዐማራ ክልል» በመባል የሚታወቀው የኢትዮጵያ ክፍል ኅልውናውን ካስቆጠረ ፳፫(ሃያ ሦሥት) ዓመታት ሆኗል። ስለዚህ ይህን ሁሉ እንዴት መካድ ይቻላል? ለፕሮፌሥር መሥፍን የክህደት መንገዳቸው ማጠናከሪያ አድርገው የሚያቀርቡት «ስለ ዐማራ አጥንቻለሁ» የሚሉት ፈሊጥ ነው። ይህ አጥንቻለሁ የሚሉት ጥናት ዕውነት ከሆነ፥ ባለፉት ዘመናት «የዐማራ ገዥ መደብ፣ ጨቋኝ የዐማራ ብሔር፣ ነፍጠኛ ዐማራ፣ የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች ደመኛ ጠላት፣ ወዘተርፈ» እየተባለ ሲወገዝና የመከራ ዓይነቶችን ሲቆጥር ለምን ዝም አሉ? ኢትዮጵያውያን ዐማሮች ከሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች፥ «አገራችሁ አይደለም እና ውጡ» ተብለው፣ ቤት ንብረታቸውን ተነጥቀው፤ ከደቡብ፣ ከሐረርጌ፣ ከአርሲ፣ ከባሌ፣ ከወለጋ፣ ከኢሉባቡር፣ ከሶማሌ፣ ከቤንሻንጉል-ጉምዝ እንዲሁም ከሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች ሲባረሩ፣ ፕሮፌሥር መሥፍን «እነዚህ እኮ ዐማራ አይደሉም፣ የሌላ ነገድ አባሎች ናቸው፤» አላሉም? «እንዲያውም ዐማራ የምትሉት ሰው በምድረ-ኢትዮጵያ የለም፤» ብለው ማስተባበል እንዴት ተሣናቸው? እነህ ሰው የሌሎችን የኢትዮጵያ ነገዶች እና ጎሣዎች ኅልው መሆን ሲቀበሉ እንዴት የዐማራ ነገድን ኅልውና ሽምጥጥ አድርገው ለመካድ ዳዳቸው? ማንን ለማስደሰት ይሆን?

በደርግ የአገዛዝ ዘመን ስለኢትዮጵያ ነገዶች እና ጎሣዎች በኢትዮጵያ የብሔረሰቦች ጥናት ተቋም በተደረጉት የጥናት ውጤቶች መሠረት፣ የዐማራ ነገድ ከኢትዮጵያ ነገዶች አንጋፋው፣ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ተሠራጭቶ የሚኖር፣ እንዲሁም በቁጥርም ከፍተኛው እንደሆነ ያሣያሉ።

ሌላው የዐማራን ነገድ ኅልውና የሚያረጋግጠው ደረቅ ማስረጃ በኢትዮጵያ የተደረጉት የሕዝብ ቆጠራ ውጤቶች ናቸው። ለምሣሌም ያህል፡- በ፲፱፻፸፮ (1976) ዓ.ም. በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ፵፪(አርባ ሁለት) ሚሊዮን ያህል እንደነበረ ይታወቃል። ከጠቅላላው የአገሪቱ ሕዝብ (42 616 876) ውስጥ የዐማራው ነገድ ተወላጆች ብዛት 12 055 250 (አሥራ ሁለት ሚሊዮን ሃምሣ አምሥት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ) ነበር። ይህም ከአጠቃላይ የአሪቱ ሕዝብ 28.288 ከመቶ እንደነበረ ያሣያል። በሥርጭት ረገድም፥ በሸዋ 23.1 በመቶ፣ በአዲስ አበባ 47.86 በመቶ፣ በወሎ 79.86 በመቶ፣ በጎንደር 84.83 በመቶ፣ በጎጃም 87.58 በመቶ፣ የዐማራ ነገድ ተወላጆች ነበሩ፣ በግለሰብ ደረጃም ሰዎች ማንነታቸውን «ዐማራ ነን» ብለው ማረጋገጣቸው በውል ታይቷል። ዐማራው በሌሎች የአገሪቱ ክፍለ-ሀገሮችም በበቂ መጠን ተሰራጭቶ እንደሚገኝ የቆጠራው ውጤት አሣይቷል። በዚህም መሠረት በሐረርጌ፣ በሲዳሞ፣ በከፋ፣ በወለጋ፣ በጋሞጎፋ፣ በባሌ፣ በአርሲ እና በአሰብ የዐማራው ነገድ ተወላጆች ብዛት ከ1.2 ሚሊዮን በላይ እንደነበረ መረጃው ያስረዳል። በዚያ የሕዝብ ቆጠራ ውጤት የኦሮሞን ቁጥር ከፍ፣ የዐማራን ቁጥር ግን ዝቅ ለማድረግ ሆን ተብሎ የቁጥሮች ጨዋታ የተሠራ መሆኑ ቢታወቅም፣ ዐማራው በቁጥር በአገሪቱ ከሚገኙ ነገዶች እና ጎሣዎች በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል (ማዕከላዊ የስታትስቲክስ ባለሥልጣን፣ ታኅሣሥ ፲፱፻፹፫ (1983) ዓ.ም.)።

በሁለተኛ ደረጃ በ፲፱፻፹፯(1987) ዓ.ም. በተደረገ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 53 499 248 መሆኑ ተገልጿል። ከዚህ ውስጥ 13 834 297 ያህሉ ዐማሮች መሆናቸውን ያሣያል። በንፅፅር ሲታይ በትግሬ-ወያኔ ዘመን በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት በ፲(አሥር) ዓመታት ውስጥ የዐማራ ነገድ ተወላጆች ቁጥር የጨመረው በ1,779,047 ብቻ ነው። ይህም የቆጠራው ውጤት የወያኔን ዐማራን የማጥፋት የፖለቲካ ዓላማ በጉልህ የሚያሣይ ነው። ሆኖም የዐማራ ነገድ በቁጥሩ ብቻ ሣይሆን በሥርጭትም ጭምር በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች በብዛት የሚገኝ መሆኑን የቆጠራው ውጤት አላስተባበለም። በመሆኑም ወያኔ «የዐማራ ክልል» ብሎ በከለለው ውስጥ ከሚኖረው 13 834 297 ሕዝብ መካከል ዐማራው 81.5 ከመቶ መሆኑን፣ በ«ትግራይ ክልል» ከሚኖረው 3 136 267 ሕዝብ መካከል የዐማራው ነገድ 2.6 ከመቶ በመያዝ በክልሉ በሕዝብ ብዛት በሁለተኛ ደረጃ እንደሚገኝ ታውቋል። በ«ኦሮሚያ ክልል» ከሚኖረው 18 732 525 ሕዝብ መካከል 9.1 ከመቶ የሚሆነው የዐማራ ነገድ መሆኑን እና ይህም በ«ክልሉ» ከሚኖሩት ነገዶች መካከል ከኦሮሞው ቀጥሎ

በቁጥር ከፍተኛው እንደሆነ ያሣያል። አርባ አምሥት(፵፭) ነገዶች እና ጎሣዎችን ባጠቃለለው የ«ደቡብ ክልል» ዐማራው በቁጥር በስምንተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በዚህ «ክልል» 10 377 028 ሕዝብ እንደሚኖር ቆጠራው አሳይቷል። ወያኔ «ሐረሪ» ብሎ የመንግሥትነት ዕውቂያ ከሰጣቸው ክልሎች አንዱ የሆነው የሕዝቡ ቁጥር 131 139 ነው። ከዚህ የ«ሐረሪ ክልል» ነዋሪ ሕዝብ መካከል 52.3 ከመቶው ኦሮሞ ሲሆን፣ 32.6 ከመቶው ዐማራ ነው። ሐረሪዎቹ 7.1 ከመቶ ብቻ ናቸው። እንግዲህ ለእነዚህ አናሣ ቁጥር ለያዙት ነው የአብዛኛውን የኦሮሞ እና የዐማራ ነገዶች ተወላጆች ዕጣ ፋንታ እንዲወስኑ ወያኔ የመንግሥትነት መብት የሰጣቸው። ይህንንም «ዲሞክራሲ ነው» እያሉን ነው። በሶማሌ ክልል 3 439 860 ሕዝብ እንደሚኖር በ፲፱፻፹፱(1989) ዓ.ም. የተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ያመለክታል። ከዚህ መካከል በዚያ ክልል ዐማራው 0.69 ከመቶ በመያዝ በሦስተኛነት ደረጃ ላይ ይገኛል። ለሁሉም ሚዛናዊ ፍርድ ለመስጠት እንዲቻል የሚከተለውን ሠንጠረዥ እንመልከት።

**<u>በ፲፱፻፹፯(1987) እና በ፲፱፻፹፱(1989) ዓ.ም. በተደረጉት የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ውጤቶች *መሠረት የክልሎችና የአስተዳደሮች ሕዝብ የብሔር /ብሔረሰብ ሥርጭት እና ብዛት</u>**

| ክልል ወይም አስተዳደር | የክልሉ ሕዝብ ብዛት | ከአገሪቱ ሕዝብ (በመቶኛ) | በክልሉ የሚኖሩ ብሔር/ብሔረሰቦች | የየብሔረሰቡ ብዛት | ከክልሉ ሕዝብ (በመቶኛ) | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 3 136 267 | 5.6 | ትግሬ | 2 971 738 | 94.75 | ከ10 ሺህ ሕዝብ በላይ ያላቸው |
| | | | ዐማራ | 81 297 | 2.59 | |
| | | | ሣሆ/ ኢሮብ | 22 858 | 0.73 | |
| አፋር | 1 060 573 | 1.99 | አፋር | 968 018 | 91.27 | ከ2 ሺ. በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | ዐማራ | 46 534 | 4.39 | |
| | | | አርጎባ | 9 673 | 0.91 | |
| | | | ትግሬ | 8 460 | 0.8 | |
| | | | ኦሮሞ | 8 055 | 0.76 | |
| ዐማራ | 13 834 297 | 25.91 | ዐማራ | 12 615 160 | 91.19 | ከ20ሺ. በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | አገው | 417 373 | 3.02 | |
| | | | ኦሮሞ | 416 883 | 3.01 | |
| | | | ቅማንት | 172 291 | 1.23 | |
| | | | ትግሬ | 44 609 | 0.32 | |
| | | | አርጎባ | 37 626 | 0.27 | |
| ኦሮሞ | 18 732 525 | 35.1 | ኦሮሞ | 15,709 474 | 83.86 | ከ50 ሺ. በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | ዐማራ | 1 684 128 | 8.99 | |
| | | | ጉራጌ | 246 895 | 1.32 | |
| | | | ጌዲኦ | 180 215 | 0.96 | |
| | | | ሶማሌ | 107 811 | 0.56 | |
| | | | የም | 103 823 | 0.55 | |
| | | | ትግሬ-ወርጂ | 67 456 | 0.36 | |
| | | | ኩሎ | 67489 | 0.36 | |
| ሶማሌ | 3 198 514 | 5.99 | ሶማሌ | 3 011 453 | 94.15 | ከ3 ሺ. በላይ ሕዝብ የያላቸው |
| | | | ኦሮሞ | 70 506 | 2.21 | |
| | | | ዐማራ | 20 951 | 0.66 | |
| | | | ጉራጌ | 4 085 | 0.13 | |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | 464 590 | 0.86 | ጀብላዊ | 115 602 | 25.12 | ከ10 ሺ. በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | ጉምዝ | 107 495 | 23.35 | |
| | | | ዐማራ | 102 061 | 22.17 | |
| | | | ኦሮሞ | 58 833 | 12.78 | |
| | | | ሽናሻ | 32 105 | 6.97 | |
| | | | አገው | 17 928 | 3.89 | |
| ደቡብ ብሔር/ ብሔረሰቦች | 10 377 028 | 19.43 | ሲዳማ | 1 820 030 | 17.539 | ከ50 ሺ. በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | ጉራጌ | 1 646 925 | 15.871 | |
| | | | ወላይታ | 1 210 235 | 11.662 | |
| | | | ሐዲያ | 874 468 | 8.427 | |
| | | | ጋሞ | 679 540 | 6.549 | |
| | | | ከፊቾ | 521 223 | 5.023 | |
| | | | ጌዴኦ | 549 351 | 4.423 | |
| | | | ከምባታ | 459 351 | 4.423 | |
| | | | ዐማራ | 443 525 | 4.274 | |
| | | | ኩሎ | 312 929 | 2.631 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጎፋ | 273 089 | 2.320 | |
| | | | ኦሮሞ | 240 749 | 1.986 | |
| | | | ቤንች | 206 244 | 1.663 | |
| | | | ኦሪ | 17 ,611 | 1'488 | |
| | | | ኮንሶ | 154 381 | 1.362 | |
| | | | አላባ | 141 375 | 1.132 | |
| | | | ኮይራ | 117 449 | 1.014 | |
| | | | ጠምባሮ | 105 244 | 0.818 | |
| | | | የም | 84 918 | 0.586 | |
| ጋምቤላ | 181 862 | 0.39 | ኑዌር | 64 473 | 35.452 | ከ5 ሺ በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | አኙዋክ | 44 581 | 24.513 | |
| | | | ዐማራ | 12 566 | 6.909 | |
| | | | ኦሮሞ | 10 543 | 5.797 | |
| | | | ከፊቾ | 6 783 | 3.729 | |
| ሐረሪ | 138 864 | 0.06 | ኦሮሞ | 68 564 | 49.375 | ከ2 ሺ በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | ዐማራ | 42 781 | 30.808 | |
| | | | ሐረሪ | 9 374 | 6.750 | |
| | | | ጉራጌ | 4 140 | 2.981 | |
| | | | ትግሬ | 2 244 | 1.626 | |
| | | | ሶማሌ | 2 199 | 1.583 | |
| አዲስ አበባ | 2 122 737 | 0.45 | ዐማራ | 1 019 729 | 48.038 | |
| | | | ኦሮሞ | 406 598 | 19.154 | |
| | | | ጉራጌ | 310 157 | 14.611 | |
| | | | ትግሬ | 161 524 | 7.609 | |
| | | | ጋሞ | 19 855 | 0.935 | |
| | | | ዶርዜ | 19 546 | 0.921 | |
| | | | ወላይታ | 10 649 | 0.502 | |
| ድሬደዋ | 251 864 | 0.45 | ኦሮሞ | 128 896 | 48.00 | ከ3 ሺ በላይ ሕዝብ ያላቸው |
| | | | ዐማራ | 69 798 | 27.713 | |
| | | | ሶማሌ | 35 046 | 13.915 | |
| | | | ትግሬ | 4 451 | 1.767 | |
| | | | ሐረሪ | 4 222 | 1.676 | |

**ምንጭ፡- ተከሌ የሻው፣ 2000 ዓ.ም. ፣ ከገፅ 399-401፤ ማዕከላዊ የስታትስቲክስ ባለሥልጣን፣ ታኅሣሥ 2001 ዓ.ም.።**

በትግሬ-ወያኔ የአገዛዝ ዘመን ለሁለተኛ ጊዜ በ፲፱፻፺፱(1999) ዓ.ም. በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት የዐማራ ነገድ ተወላጆች ብዛት 19,867,817 መሆኑን ይጠቁማል። እንዲያውም በስታስቲክስ ባለሥልጣን ሥራአስኪያጅ ቃል መሠረት በዚያ የቆጠራ ውጤት ከ2 500 000(ሁለት ሚሊዮን አምሥት መቶ ሺህ) የማያንሱ ዐማሮች ከቁጥር መጉደላቸውን ጠቁማለች። ለዚህ የሠጠችው መላምት «ዐማራው በኤች.አይ.ቪ.-ኤድስ በሽታ በብዛት ስላለቀ ይሆናል» የሚል ነው። የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ዐማራውን በተለያዩ መንገዶች ከምድረ-ገፅ ለማጥፋት የሚያደርገው የዘር ማጥፋት ድርጊት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለፕሮፌሠር መሥፍን ይህ በአደባባይ ያገጠጠ ሃቅ አልታያቸው ያለበት ምክንያት ግን ትልቅ እንቆቅልሽ ነው።

## ፪ኛ. የአማርኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ከሚነገሩት ቋንቋዎች መካከል በቀዳሚነት የሚገኝ መሆኑ

እያንዳንዱ ሰው በርካታ የማንነት መገለጫዎች እንዳሉት ይታወቃል። ለምሣሌ፥ የስም፣ የፆታ፣ የኃይማኖት፣ የሙያ፣ የቀለም፣ የማኅበር፣ የዜግንነት፣ የቡድን፣ የፖለቲካ፣ የሥራ፣ የዘር፣ ወዘተርፈ ማንነቶች አሉት። አንዳንዶቹ የማንነት መታወቂያዎች ሊለወጡ የሚችሉ እና በሌሎች ማንነቶች የሚተኩ የሚችሉ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ የማይለወጡ ናቸው። ምንም እንኳን ዛሬ በምንኖርበት የቴክኖሎጂ ዘመን «አይለወጥም» የምንለው ነገር ተለዋዋጭ መሆኑን በፆታዎች ለውጥ እያየን ቢሆንም፣ ለውጡ መሠረታዊ የሆነውን ተፈጥሮን ፈጽሞ የማይተካ በመሆኑ፤ የፆታ፣ የቀለም፣ የዘር፣ ማንነቶችን ፈጽሞ መለወጥ አይቻልም። ስለሆነም የሰዎች የማንነት መታወቂያ ከሆኑት አንዱ እና ግዙፉ የቋንቋ ማንነታቸው ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ራሳቸውን በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪነት የሚገልጹ አያሌ ሰዎች አሉ። እነዚህም ሰዎች «ዐማራ» በተሰኘ ነገድ የተጠቃለሉ ናቸው። አማርኛ ቋንቋ ከዐማራ ነገድ አልፎ የኢትዮጵያ ነገዶች እና ጎሣዎች መግባቢያ ከሆነ ዘመናት የተቆጠሩለት፣ በአፍሪቃ አኅጉርም ብቸኛ የሆነ የራሱ ፊደል ያለው ቋንቋ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት በዓለም ላይ በሥርጭቱ ከፍተኛውን መጠን የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሲተረጎም ከግዕዝ ቀጥሎ ቀድሞ የተተረጎመው በአማርኛ ነው። ይህም የሚያመለክተው የቋንቋው ባለቤት፣ የራሱን ማንነት በሚናገረው ቋንቋ የሚገልጽ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ መኖሩን የሚያመለክት ነው። በዚህም መሠረት የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር እ.ኤ.አ. ከ፲፰፻፲፯(1817) እስከ ፲፰፻፴፫(1833) በነበሩት ፲፯(አሥራ ሰባት) ዓመታት ውስጥ 10,016 (አሥር ሺ አስራ ስድስት) ቅጂዎች፣ ከ፲፰፹፪(1882) እስከ ፲፱፻፯(1907) በነበሩት ፳፮(ሃያ ስድስት) ዓመታት ውስጥ 18,560(አሥራ ስምትንት ሺ አምስት መቶ ስድሣ) ቅጂዎች፣ ከ፲፱፻፱(1909) እስከ ፲፱፻፳፯(1927) በነበሩት ፲፱(አሥራ ዘጠኝ) ዓመታት ደግሞ

89,487(ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ ሰማኒያ ሰባት) ቅጂዎች፣ በጠቅላላው 118,063 (አንድ መቶ አሥራ ስምንት ሺህ ስድሣ ሦሥት) ቅጂዎች በአማርኛ ቋንቋ አሣትሞ አሰራጭቷል። (ዶክተር ላጲሶ ጌታሁን ደሌቦ ፲፱፻፹፫(1983) ዓ.ም.፣ ገፅ 112)። ይህ ሁሉ የዐማራ ነገድ በሌለበት የተከናወነ አይደለም። የነገዱ መኖር የቋንቋውን መኖር ሲያሳይ፣ ቋንቋው ደግሞ ከ፫፻፳(320) ዓ.ም. ጀምሮ በጽሑፍ ላይ የዋለ በመሆኑ ማደጉን እና መሥፋፋቱን ያመለክታል። ከሁሉም በላይ አማርኛ ቋንቋ ከዐፄ ኢዛና ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የራሱን ፊደል ቀርፆ የሕዝብ እና የመንግሥት የሥራ ቋንቋ በመሆን የአገሪቱ ባህል፣ ታሪክ፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ ወዘተርፈ የሚተነተንበት፤ በውጭ አገር ቋንቋዎች የተጻፉ መጻሐፍት የተመለሱበት፤ ከኢትዮጵያ አልፎ የአሜሪካ የተባበሩት ግዛቶች ዋና ከተማ በሆነችው በዋሽንግተን ዲሲ በአምስተኛ ደረጃ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ ለመሆን የበቃ ነው። ይህ ሁሉ ያለ ዐማራ መኖር የሚታሰብ አለመሆኑን ማንም ንፁህ አዕምሮ እና አስተዋይ ልቦና ያለው ሰው ይስተዋል አይባልም።

ሻለቃ ደማ ዘንግእዜር (ዘብሔረጉራጌ) «ኅብረ ሰዋሰው »በተሰኘው_መጽሐፋቸው እንደሚገልፁት ደግሞ፣ የአማርኛ ቋንቋ «ከልደት በፊት በ፩ሺህ፸፩(1071) ዓመተ-ዓለም በዘመነ መንግሥት አፄ (ጥኖተ) ሴም ኢትዮጵያዊ አስተዳደር፣ ከግዕዝ ሁለተኛ ሆኖ ሲነገር የኖረ ፫ሺህ፳፩(ሦሥት ሺህ ኻያ አንድ) ዓመት ያህል እድሜ ያለው፤ ጥሩ፣ አንደበት የማይዝ፣ ሚሥጢረ ብዙ፣ የሠመረ፣ የነገድ ቋንቋችን ነው።» (ደማ ዘንግእግዜር፣ ፲፱፻፶፬(1954) ዓ.ም.፣ ገፅ 8) ሲሉ የቋንቋውን ዕድገት፣ ለአንደበት ምቹ፣ ለአእምሮ የሚስማማ፣ ለጆሮ የሚጥም መሆኑን እና የረዘመ ታሪክ እንዳለው ከነገዱ ማንነት ጋር አያይዘው ገልጸውታል።

የኢትዮጵያን ነገዶች እና ጎሣዎች ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ አንድነት እና ልዩነት፣ ትሥሥር እና ቁርኝት ያጠኑት አሜሪካዊው ፕሮፌሠር ዶናልድ ሌቪን «ትልቋ ኢትዮጵያ» በሚለው መጽሐፋቸው፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአምስት ዋና የተበታተኑ ነገዶች/ጎሣዎች ሲመድቡ አንደኛው ሴሜቲክ(የሴም) የሚለው ነው። በዚህ የቋንቋ ግንድ ከተጠቃለሉት የሴማዊ ቋንቋ ቤተሰቦች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነው የዐማራ ሕዝብ ይገኝበታል። ዶናልድ ሌቪን የዐማራ ነገድ ከመኖር አልፎ ኃይማኖታዊ፣ ፖለለቲካዊ እና አስተዳደራዊ ሥርዓት ዘርግቶ የኖረ እንደሆነ አጉልተው ገልፀውታል። ዶናልድ ሌቪን የዐማራ እና የኦሮሞ ልማዳዊ የማኅበረሰብ መዋቅር ገፅታዎችን እና ታሪካዊ ክንዋኔዎችን ባመዛዘኑበት ሥንጠረዥ፥ የዐማራው የግንኙኝት ባሕርይ ሥርዓት እርከናዊ እና ግለሰባዊ፤ የተቋም አመዳደቡ በፖለቲካ እና በባህል መስክ ራስ-ገዝ፤ የማኅበረሰቡ ዓላማ፣ ማለትም፡- የማኅበረሰቡ ማንነት እና ታሪካዊ መርኃግብሩ የነገደ-ብዙኃንን ንጉሣዊ ግዛት ማስፋፋት፣ የሥርዓቱ ዕርጋታ ከፍተኛ የሆነ ሲሉ ገልጸውታል። በተመሳሳይ መንገድ ከ፲፩ኛው እስከ ፲፮ተኛው ምዕተ ዓመት የዐማራ መስፋፋት የተከናወነበት፤ ይህም በፖለቲካ ጫና ችሎታ እና ብርታት የተከወነ እንደነበረ፣ ከ፲፯ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ እስከ ፲፱ኛው መቶ መጀመሪያ ድረስ የኦሮሞ ድሎች የተስፋፉበት ዘመን እንደነበረ እና ይህም በወቅቱ በነበረው የኦሮሞዎች የውትድርና ችሎታ እንደሆነ መዝግበዋል። ከ፲፱ኛው ምዕተ ዓመት መገቢያ ጀምሮ ዐማራው እንደገና መነሳቱን እና ያጣውን የበላይነት ያስመለሰበት ሁኔታ መከሰቱን ገልጸው፤ የዚህም መሠረታዊ ምክንያት ዐማራው ከውድቀት መልሶ የማንሰራራት ችሎታ ያለው መሆኑን አብራርተዋል (ሚሊዮን ነቅንቅ (ትርጉም) ፲፱፻፺፫(1993) ዓ.ም. ፣ ገፅ 134)። እንግዲህ ከነባራዊ ታሪካዊ ሁኔታው መገንዘብ የሚቻለው፣ ዐማራው በነገድነት ከመኖር አልፎ የኢትዮጵያን ዕጣ ፋንታ በመወሰን ደረጃ ሠፊ ሚና የተጫወተ መሆኑን ነው።

## ፫ኛ. የጽሑፍ፣ የድምፅ(የቃል) እና የምሥል ማስረጃዎች

በኢትዮጵያ ዐማራ የተሰኘ ነገድ በስፋት እንዳለ እና ይህም ነገድ «ሌሎችን ነገዶችን እና ጎሣዎችን ለረጅም ዓመታት ጨቁኖ የገዛ ነው፤» ተብሎ በታሪካዊ ጠላቶቹ ይወገዛል። ከዚህም አልፎ፥ «አድሐሪ፣ በዝባዥ እና በኢትዮጵያ ለተፈጠሩ ሁለንተናዊ ችግሮች ሁሉ ተጠያቂ ነው፤» የሚሉ ክሶች ከተማሪዎች እንቅስቃሴ መግለጫዎች እስከ የተለያዩ የ«ብሔር ነፃ አውጭ» ድርጅቶች ሰነዶች ድረስ ይወነጀላል። ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ሰነዶች «ዐማራ» የተሰኘ ነገድ ከመኖሩም በላይ ገዥና አስገባሪ እንደነበር ያረጋግጣሉ፣ ይከሣሉ። ከሁሉም በላይ የሕወሓት ፕሮግራም «የትግራይ ሕዝብ ደመኛ ጠላት ዐማራው ነው፤» በማለት የትግራይ ሕዝብ ዐማራውን ታግሎ እንዲያጠፋ ኃሣብ አመንጭቷል። ያመነጨውንም ኃሣብ ባለፉት ፵(አርባ) ዓመታት በተግባር ላይ በማዋል ላይ ይገኛል። የትግሬ-ወያኔ ከኦነግ እና መሠል ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ዐማራ ኃይሎች ጋር በማበር በበደኖ፣ በአርባጉጉ፣ በአሰቦት ገዳም፣ በወተር፣ በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በጠለምት፣ በሡቲት፣ በአሶሳ፣ በምሥራቅ ወለጋ፣ በመተከል፣ በኢሉባቡር፣ ወዘተርፈ ይኖሩ በነበሩ የዐማራ ነገድ ተወላጆች ላይ የፈፀሟቸው የዕልቂት ድርጊቶች የዚህ ፖሊሲ ቀጥተኛ ውጤቶች ናቸው። ዐማራው ከሶማሌ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ፣ ከቤንሻንጉል-ጉምዝ «ክልሎች» ኃብት ንብረቱን ተነጥቆ የተባረረው፣ ዐማራ በመሆኑ ብቻ ነው። ይህን ካለፕሮፌሠር መሥፍን በቀር የሚያስተባብል ወይም የሚክድ ሰብዓዊ ፍጡር የለም።

የፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም የሁለት ወራት የ፫ኛ ፖሊስ ጣቢያ የእስር ጓደኛ የነበሩት፣ የ«ቀስተ ደመና» ፓርቲ መሪያቸው የነበሩት፣ የአሁኑ የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የሚመሠክሩባቸው ሌላም ሃቅ አለ። ዶክተር ብርሃኑ በሚመሩት የግንቦት 7 ድምፅ በሆነው ጋዜጣ ጥቅምት ፳፯(ሃያ ሰባት) ቀን ፪ሺህ፩(2001) ዓ.ም. በቁጥር ፳፭(ሃያ አምሥት)፣ ዕትሙ **«አባማ ተመረጡ፤ አለም ተደሰተ፣ የኢትዮጵያ አምባገነን ግን ሃዘን ተቀምጧል»** በሚል ርዕስ ባሠፈረው ርዕሰ አንቀፁ፣ የዐማራ ነገድ መኖሩን ብቻ ሣይሆን፣ ለዘመናት ገዥ ሆኖ መኖሩን በሚከተለው መልኩ ዘግቦታል፡-

> **«ከትናንት በስቲያ በባርነት ሲሸጡ ሲለወጡ የነበሩ ጥቁሮች ዛሬ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት መመረጥ ከቻሉ፣ በሀገራችን ኢትዮጵያም ለአስርተ መቶዎች አመታት እየተፈራረቀ ሲገዛ የኖረው የአማራና ትግሬ ልሂቅ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት እስከሆነ ድረስ፣ ቦታውን ለደቡቡም፣ ለኦሮሞውም፣ ለአኝዋኩም፣ ለመልቀቅ ፈቃደኛ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም።»**

ሲል የገለጸው ነገዱ በዕውን ያለና ሲገዛም እንደነበር የሚያረጋግጥ ምስክርነት ነው። **ይህን አባባል ግን ሞረሽ-ወገኔ እንዳለ አይቀበለውም። ምክንያቱም በማንኛውም የታሪክ ዘመን ዐማራው በብቸኝነት ኢትዮጵያን የገዛበት ሁኔታ ስለሌለ፣ የታሪክ መፉለስ ብቻ ሳይሆን፣ የግንቦት 7 አቋም ፍፁም ውሸት በመሆኑ ነው። በመሠረቱ በኢትዮጵያ ዘለቄታዊነት ያለው ሰላም ለማስፈን ትግሉ መደረግ ያለበት ፍትኅን መርሆው ላደረገ ለተሻለ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ሥርዓት ግንባታ እንጂ፤ ግንቦት 7 እንደሚለው ገዥዎችን ለማፈራረቅ ከሆነማ የጠገበ ጅብ አባርሮ የተራበ ጅብ ግባ ማለት ይሆናል። ይህ ደግሞ ለማንም አይበጅም።**

ፕሮፌሠር መሥፍን በዚህ ቃለ-ምልልሳቸው «ዐማራ የሚባል ነገድ የለም» ከማለት በላይ ዘልለው እና ተሻግረው፥ «በበደኖ እና አርባጉጉ የተጨፈጨፉት ዐማራዎች ሳይሆኑ አሮሞዎች ናቸው» ብለዋል። ወያኔ ቁሞ «በሏቸው» እያለ፤ የኦነግ መሪዎች እነ ሌንጮ ለታ፣ አብዩ ገለታ፣ ዳውድ ኢብሣ፣ ወዘተርፈ ያስፈፀሙትን፤ የኦሕዴድ መሪዎች እነ ኩማ ደመቅሣ፣ አባ ዱላ ገመዳ፣ ሐሰን ዓሊ፣ ወዘተርፈ የጥፋቱ

*አዝማቾች ሆነው ሣለ፤ ዘር እየተለየ የተገደሉትን ዐማሮች «ኦሮሞዎች እንጂ ዐማሮች አይደሉም» በማለት ፕሮፌሠር መሥፍን ምን ጥቅም ለማግኘት በዚህ ዕድሜያቸው ክህደትን እንደመረጡ «እንዲህ ነው» ለማለት ግራ ያጋባል። ተጨፍጫፊዎቹ ዐማሮች ስለመሆናቸው አባ ኒቆዲሞስ የሰጡትን የዐይን ምሥክርነት፣ እንዲሁም ወያኔ ለራሱ ፖለቲካ ፍጆታ ሲል ከኦነግ ጋር ኢትዮጵያን በጋራ ለማጥፋት የተዋዋለውን ስምምነት በመካዱ ኦነግ ሲያፈነግጥ ያወጣው በቪዲዮ የተደገፈ መረጃን፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ትውልዶች ፈጽመው ያልጠፉ ስለሆነ፤ በእነርሱ ነቃሽነት የፕሮፌሠር መሥፍን የክህደት ቃል እርቃኑን የሚቆም የውሸት እና የሽፍጥ ገለባ ክምር መሆኑን ኢትዮጵያዊው ሁሉ ይስተዋል አይባልም።*

*የፕሮፌሠር መሥፍን «የክህደት ቁልቁለት» «በዕንቁላሉ ጊዜ በቀጣሽኝ» ዓይነት ሆኖ፣ ከመጀመሪያውም ሳይቀጡ በጋጠወጥነት ያደጉ በመሆናቸው፤ አባታቸውን ሊቁን አለቃ አስረስ የኔሰውን በመካድ የጀመሩት ክህደት፣ ይኸውና የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ከሆኑት ታላላቅ ነገዶች ውስጥ አንዱ እና ግንዱ የሆነውን የዐማራ ነገድ «የለም» እስከማለት አደረሣቸው። ፕሮፌሠር መሥፍን «ዐማራ የሚባል ነገድ የለም» ባሉበት በዚህ ቃለ-ምልልስ «የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔን የመሠረትኩበት ዋናው ምክንያቴ ወያኔዎች ዲሞክራት ናቸው፣ ለዲሞክራሲ ይሠራሉ የሚል ዕምነት ይዤ፣ እነርሱን ለማገዝ፣ ለመርዳት አስቤ ነበር፤» ሲሉ ተደምጠዋል። ልብ በሉ! «የተሟላሁ ምሁር ነኝ፤ ካለ እኔ ማንም በኢትዮጵያ ጉዳይ የሚያውቅ የለም፤» የሚሉት ፕሮፌሠር መሥፍን፣ በወያኔ የሽግግር መንግሥቱ ቻርተር ኤርትራ ተገንጥላ፣ አገሪቱ ወደብ-አልባ ሆና፣ የሕዝቡ ነባር አንድነት እንዲሰባበር የጎሣ ፖለቲካ ርዕዮት ሆኖ በሚቀነቀንበት ወቅት «ወያኔ ዲሞክራት ነው» ብለው ያምኑ እንደነበር የሚያረጋግጥ አባባል ነው። ይህም ፕሮፌሠር መሥፍን  የዐማራው ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያዊነት አውራ ጠላት መሆናቸውን በተጨባጭ የሚያሳይ ማስረጃ ነው። አገር እና ሕዝብ ሳይኖር ዲሞክራሲን የት ላይ ሊዘሩት እና ፍሬውን ለመልቀም አስበው ይሆን?*

*የትግሬ-ወያኔዎች «ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም፤ በኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት የተያዘች አገር ናት፤ ኤርትራ እና ኢትዮጵያ በአንድ ወቅት በተሠራ የታሪክ ስህተት አንድ አገር የሆኑ ናቸው፤» ብለው ለ፲፯(አሥራ ሰባት) ዓመታት ጠብመንጃ ነክሰው፣ ከሻዕቢያ በላይ ኤርትራዊ ሆነው፣ ኤርትራን ያስገነጠሉ እና የአገሪቱን የተፈጥሮ የባሕር በር ያዘጉ ሰዎች በምን ተዓምር ዲሞክራቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ እና ለኢትዮጵያ አሣቢዎች እነርሱ ብቻ መሆናቸው የተገለፀላቸው ምሁር ፕሮፌሠር መሥፍን ወልደማርያም ብቻ ናቸው። ስለሆነም የእርሳቸውም ዕውቀት ደጋግመን እንደምናየው ከክሕደት ያለፈ አይደለም።*

*ፕሮፌሠር መሥፍን ዛሬ ብቻ ሣይሆን ቀደም ሲልም ጀምሮ የኢትዮጵያዊነት እና የዐማራው አውራ ጠላት የጭቃ እሾህ ሆነው የዘለቁ መሆናቸውን ከሚያሳዩት ዕርምጃዎቻቸው አንዱ ይህ «ዐማራ የለም» የሚለው አቋማቸው ነው። ሌላው በንጉሠ ነገሥቱ ባለሥልጣኖች ላይ የሰጡት አስተያየት እና የእርሳቸውን አስተያየት ተከትሎ በ፷(ስድሣዎቹ) የአገር ራሶች ላይ የተወሰደው የኢትዮጵያ ጥፋት አሃዱ ብሎ የተጀመረበት ድርጊት ነው። ማንም የዚያን የአብዮት አፍላ ወቅት ይከታተል የነበረ ሁሉ እንደሚያስታውሰው፣ ከተወሰዱት ርምጃዎች መካከል «በሕዝብ እና በአገር ላይ ጉዳት ያደረሱ ባለሥልጣኖች ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኙ፤» በሚል ጉዳዩን ተከታትሎ የሚያስፈጽም አጣሪ(መርማሪ) ኮሚሽን ተቋቁሞ ነበር። ኮሚሽኑን ከሚመሩት ሰዎች መካከል አንደኛ ኤርትራዊው በረከት ኃብተሥላሴ የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፣ ሁለተኛ ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደ ማርያም ምክትል ሰብሳቢ፣ ሆነው መሾማቸው ይታወቃል። የለውጡ ሂደት እየፈጠነ ሲሄድ ግራ የተጋባው የደርግ አመራር ለኮሚሽኑ በቁጥጥር ሥር የዋሉትን የቀድሞውን ባለሥልጣኖች ጉዳይ በቶሎ አጣርቶ ለፍርድ እንዲያቀርብ ሲጠይቅ፣ ፕሮፌሠር መሥፍን የሰጡት መልስ «ነገሩ በሕግ ይታይ ከተባለ ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ይህ ደግሞ የራሳችሁን መኖር ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው። ከስፔን አብዮት ምን ትማራላችሁ? በእኔ በኩል መፍትሔው ያለው በእጃችሁ ነው።» ሲሉ በትረ-ሥልጣኑን ጨምድዶ ለመያዝ ፍላጎታቸው ለሆኑት እና ያንን ሥልጣን የሚነጥቃቸው ኃይል ካለ ማናቸውንም ዓይነት ዕርምጃ ለመውሰድ የማያወላውል አቋም ላላቸው ወታደሮች ውሣኔ-አዘል ምክር ሰጡ። «ለብልህ አይነግሩ፣ም ለአንበሣ አይመትሩም፤» የሆነላቸው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ከፕሮፌሠር መሥፍን በተነገራቸው የማስፈራሪያ የምክር ቃል በመነዳት ኅዳር ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. (ኅዳር 13 ቀን 1967 ዓ.ም.) ሌሊት ፷(ስድሣ) አዛውንቶችን በመትረየስ አስረሸኑ። ለመሆኑ ፕሮፌሠር መሥፍን ወልደማርያም እነዚህን የአስተዳደር፣ የዲፕሎማሲ፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ አመራር ልምድ እና ሙያ ያካበቱ እና በተለያዩ ደረጃዎች ኢትዮጵያን ያገለገሉትን ኢትዮጵያውያን አባቶች አገሪቱ እንድታጣ ያደረጉ ክፉ መካሪ መሆናቸውን ስንቶቻችን እናውቅ ይሆን?*

*ለማጠቃለል፦ የፕሮፌሠር መሥፍን ወልደማርያም የሰሞኑ «ዐማራ የሚባል የለም» የሚለው የክህደት አቋማቸው ዛሬ በድንገት የተገለፀላቸው ዕውቀት ሣይሆን፣ ለረዥም ዘመን ሲያራምዱት የቆዩት አቋማቸው መሆኑን ማስታወስ ያሻል። ይህም ዐማራውን ከምድረ-ገፅ ለማጥፋት ለሚንቀሣቀሱት ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ዐማራ የጥፋት ኃይሎች ተጨማሪ ነዳጅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ በተለይም ዐማራው፣ ተመጣጣኝ የሆነ የአፀፋ መልስ ሊሠጣቸው ይገባል ብለን እናምናለን።*

***ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደጋለን!***

***ፈለገ-አሥራት የትውልዳችን ቃልኪዳን ነው!***

***ኢትዮጵያ በጀግና እና ቆራጥ ልጆቿ መስዋዕትነት ታፍራ እና ተከብራ ለዘለዓለም ትኖራለች!***